# የአራት አባቶች ወግ

አራት አባቶች ሻይ ቢጤ ይዘው ሲጨዋወቱ ቆይተው ከቡና ቤቱ እየወጡ ሣለ አንደኛው አባት ሂሳብ ሊዘጋ ወደ ኋላ ቀረ። ሧስቱ እየተጨዋወቱ መንገዳቸውን ቀጠሉ። አንደኛው አባት ስለ ልጁ ጥሩ ቦታ መድረስ እየተኩራራ ሲናገር፦

"የኔ ልጅ በጣም ጎበዝና ታዋቂ ሕናጻ ተቋራጭ ነው። ከሃብቱ መብዛት የተነሳ ለአንዱ ጓደኛው ትልቅ ቪላ ሰርቶ በነጻ ሰጠው።" ይላቸዋል።

ሌላኛውም ቀጠል አድርጎ "የኔስ ልጅ በጣም ታዋቂ የመኪና መገጣጠሚያ ካምፓኒ አለው ።ብታምኑም ባታምኑም ለጓደኛው አዲስ ማርቸዲስ መኪና በነጻ ሰጠው።" ብሎ የበኩሉን ይገልጻል።

ሧስተኛውም በመቀጠል "የኔም ልጅ የራሱ ባንክ ያለው ታዋቂ ሃብታም ነው። ትናትና ለጓደኛው 10 ሚሊዎን ዶላር ሲሰጠው 10 ብር የሰጠው ያህል አልተሰማውም።" በማለት ሁሉም የልጃቸውን ጉብዝና ገልጸው እንዳበቁ ያ የሻይ ሂሳብ ሊከፍል ወደ ኋላ የቀረው አራተኛው አባት ይደርስባቸውና ይቀላቀላቸዋል።

እየተጓዙ ይጨዋወቱ ከነበሩት አንደኛው አባት አሁን የመጣውን አባት "አንተ ከመምጣትህ በፊት ስለ ልጆቻችን ነበር የምናወራው ያንተስ ልጅ እንዴት ነው?" ብሎ ይጠይቀዋል።

አራተኛውም አባት "አይ _ _ _ የኔ ልጅ እንኳ ጌይ (ግብረ ሰዶማዊ) በመሆኑ በጣም ነው የማፍርበት ግን የሚገርማችሁ በዚሁ በብልጋናው ተከኖበታል መሰለኝ። አንደኛው ውሽማው ቪላ ቤት ሡርቶ ሰጠው። ሌላው ደግሞ ማርቸዲስ መኪና ሲሰጠው ይባስ ብሎ ሧስተኛው ውሽማ ደግሞ ትናትና 10 ሚሊዮን ዶላር ሰጥቶት ይምነሽነሻል እላችኋለሁ በማለት የሁሉንም ጉድ ዘርግፎ ። አፋቸውን ዘግተው እንዳቀረቀሩ ሳይነጋገሩ ተለያዩ።